# የሄፓታይተስ B መረጃ ለእርጉዝ ሴቶች



## ሄፓታይተስ B ምንድን ነው?

- ሄፓታይተስ B የጉበት በሽታ ሲሆን የሚፈጠረውም በቫይረስ ነው። አብዛኛዎቹ በ ሄፐታይተስ B የሚያዙ ሰዎች ቫይረሱ በሰውነታቸው ውስጥ የሚቆይ ሲሆን ይህም ህይወታቸውን በሙሉ ለሚቆይ ህመም ይዳርጋቸዋል።
- ሄፓታይተስ B በጊዜ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የጤና ችግር ሊያስከትል ይችላል ይህም የጉበት መጎዳትን፣ የጉበት ስራ ማቆምን እና የጉበት ካንሰርን ጨምሮ ነው።
- አብዛኛዎቹ ሄፓታይተስ B ያለባቸው ሰዎች ምንም ምልክት የማየታይባቸው ሲሆን እንዳለባቸው ላያውቁ ይችላሉ። ነገር ግን ይህንን ሄፓታይተስ B ወደሌሎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

## እርጉዝ የሆኑ ሴቶች መመርመር ያለባቸው ለምንድን ነው?

- አንዲት እርጉዝ የሆነች ሴት ሄፓታይተስ B እንዳለበታ ተመርምራ የምታውቅ ከሆነ፣ ልጅዎ በወሊድ ጊዜ ህክምና ያስፈልገዋል። በሚወለዱበት ወቅት ህክምናውን የሚያገኙ ህጻናት በሄታይተስ B የመያዝ እድላቸው ጠባብ ነው።
- ህጻናት በ ሄፓታይተስ B በሚያዙበት ወቀት በህይወት =ዘመናቸው በሙሉ የሚቆይ ህመም ሊያስከትልባቸው =ይችላል።.
- እርጉዝ ሴቶች የ ሄፓታይተስ B ምርመራን በእያንዳንዱ የእርግዝናቸው ወቅት ሊያደርጉ ያስፈልጋል።

## እርጉዝ ሆነሽ በ ሄፓታይተስ B ከተያዝሽ ምን ማድረግ አለብሽ?

- የጤና አገልግሎት አቅራቢሽን በማግኘት ስለ ሄፓታይተስ B ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግሽ ማወቅ አለብሽ።
- ሄፓታይተስ B ወደልጅሽ እንዳይተላለፍ ይሆን ዘንድ =የሚሰጡ ህክምናዎች አሉ።
- ሄፓታይተስ B እንዳለብሽ የማታውቂ ከሆነ፣ ጤና አገልግሎት አቅቢሽ የ ሄፓታይተስ B ደም ምርመራ እንዲያደርግልሽ ጠይቂ።.

## ልጅሽ እንዳይያዝ እንዴት መከላከል ትችያለሽ?

- በእያንዳንዱ እርግዝና ወቅት የ ሄፓታይተስ B ምርመራ አድርጊ።
- ምርመራሽ ሄፓታይተስ B እንደሌለ የሚያሳይ ከሆነ፣ ስለ =ሄፓታይተስ B ክትባጥ ጠይቂ።
- ምረመራሽ ሄፓታይተስ B እንዳለ የሚያሳይ ከሆነ፣ ልጅሽ ህክምና እና ክትትል ያስፈልገዋል።:
  - ከወሊድ በኋላ ልጅሽ የተከታታይ ክትባቱን የመጀመሪያ ክፍል እና የሄፓታይተስ B ኢሚዩን ግሎቢንን (HBIG) ይወስዳል።
  - ልጅሽ ይህንን ሄፓታይተስ B ተከታታይ ክትባት መጨረስ ያስፈልገዋል።
  - ተከታታይ ከሆነው ክትባት በኋላ፣ ዶክተርሽ የደም ናሙና በመውሰድ ልጅሽ በ ሄፓታይተስ B ከመያዝ የተጠበቀ አንደሆነ ያረጋግጣል።
- ሄፓታይተስ B ቢኖርብሽም ጡት ማጥባት ትችያለሽ።

Public Health
Seattle & King County

Perinatal Hepatitis B Prevention Program

(206) 296 4774

www.kingcounty.gov/PHBPP

Adapted with permission from Minnesota Department of Health - Amharic 2018